የተጻራላበት፡በኋ፡እምነትም፡
ያመንህለት፡የዘለዓለም፡ሕይ
ወትን፡ለመውረስ፨፩ቆሮ፡፱፡፳
፭፡፳፯፡ፊል፡፫፡፲፪፡፲፬፨
ሙታንን፡በሚያነሣ፡በእግዚ
አብሔር፡ፊት፡በበኋ፡ሃይማኖ
ት፡በጳንጤኑ፡ሰው፡በጲላጦስ፡
ፊት፡ምስክር፡የሆነ፡በኢየሱስ
ክርስቶስ፡ፊት፡እንዲህ፡እስተ
ምርሃለሁ፡ዘዳግ፡፴፪፡፴፱፡ዮ
ሐ፡፲፰፡፴፯፡ና፲፱፡፲፩፨ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እስኪመጣ፡
ድረስ፡ሳታዳላ፡ይህን፡ትእዛዝ
በንጽሕና፡ትጠብቅ፡ዘንድ፨
በጊዜው፡ጊዜ፡የሚገለጥ፡እሱ
ብቻ፡ኃያል፡የሚሆን፡የተመሰ
ገነ፡የነገሥታት፡ንጉሥ፡የአማ
ልክት፡አምላክ፡የጌቶች፡ጌታ፤
ም፡፩፡፲፩፡ራእ፡፲፯፡፲፱፡ዘዳግ፡፲፡፲፯
እሱ፡ብቻ፡የማይሞት፡ዓለም፡
ሳይፈጠር፡በማይጠፋ፡ብርሃ
ን፡የነበረ፡ያየው፡ሰው፡የሌለ፡እ
ንግዲህም፡ሊያየው፡የማይችል
የሌለ፡ለዘለዓለሙ፡ክብር፡ጌት
ነት፡ኃይል፡ያለው፡አሜን፨
ዮሐ፡፩፡፲፰፨የዚህን፡ዓለም፡ባለ
ጸጎች፡እንዳይታበዩ፡የሚያል
ፈው፡ባለጸጋነታቸውንም፡እ
ንዳይታመኑ፡ምክራቸው፡ይስ
ይለን፡ዘንድ፡በለጋስነቱ፡ብዛ
ት፡ሁሉን፡በሰጠን፡በእግዚአብ

ሔር፡ይታመኑ፡እንጂ፨መዝ፡፷
፲፰ ፪፡፲፩፡ሉቃ፡፲፪፡፳፨መልካም፡
ይሠራ፡ይሠሩ፡ዘንድ፡ጽድቀ
ንም፡በመሥራት፡ይከብሩ፡ዘን
ድ፡ቀኖች፡ለጋሶች፡ለበጎ፡ሥራ
ተባባርዎች፡ይሆኑ፡ዘንድ፨
፲፱ የማያልፈውን፡ሕይወት፡ለማ
ግኘት፡ለሚመጣው፡ዓለም፡
ለራሳቸው፡በጐ፡መሠረትን፡
ይመሠርቱ፡ዘንድ፨ማቴ፡፮፡፳
፳ ጢሞቴዎስ፡ሆይ፡አደራህን፡ጠ
ብቅ፡ከንቱ፡ነገርን፡የሚያመ
ጡ፡እውነትን፡በሐሰት፡የሚያ
ርቁ፡ኃጢአተኞችን፡ተለያቸ
፳፩ ው፨እንዲህ፡ያሉ፡ሰዎች፡በሃይ
ማኖት፡ከሚገኘው፡ተስፋ፡ወ
ጥተዋልና፨ጸጋ፡ላንተ፡ይሁን
በአቴና፡የተጻፈ፡በቲቶ፡እጅ፡
ወደ፡ጢሞቴዎስ፡የተላከ፡መጀ
መርያ፡መልእክት፡ተፈጸመ፨
አስጀምሮ፡ላስጨረሰን፡ለእግ
ዚአብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይ
ግባው፨በእውነት፨አሜን፨

